# ጥያቄና መልስ ስለ ቂጥኝ

## ቂጥኝ ምንድነው?

ቂጥኝ የአባላዘር በሽታ ሲሆን በባክቴሪያ አማካኝነት ይከሰታል፡፡ በሽታው የተለያዩ አይነት ደረጃዎች ሲኖሩት ካልታከሙት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡

## ቂጥኝ እንዴት ይተላለፋል?

ቂጥኝ በብልት ፈሳሽ፣ በአፍ ወይም በፊንጢጣ ይተላለፋል፡፡ በእርግዝና ሂደት ውስጥ ከእናት ወደ ልጅ ሲተላለፍ በልጁ የመራቢያ ከአካላት ላይ ከፍተኛ ችግር ያስከትላል፡፡ የበሽታው ስጋት እንደ ህመሙ ደረጃ ይወሰናል፡፡

## የቂጥኝ ምርመራ ያስፈልገኛል?

የቂጥኝ ስርጭት ከፍተኛ ከሆነበት ሀገር የሚመጡ ከሆነ፣ የነጻ ምርመራ ይቀርብሎታል፡፡ የሚደረገው ምርመራ የደም ሲሆን ይህም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከፍተኛ የቂጥኝ ተጋላጭነት ላይ ከነበሩ፣ ነጻ ምርመራ ማግኘት ይችላሉ፡፡

ቂጥኝ ከፍተኛ ሁኔታ ካለበት ቦታ ከመጡ፣ ቂጥኝ ቢኖርቦትም ባይኖርቦትም ምርመራ ማድረግ ያስፈልጎታል፡፡ ይህ በተለይ ለእርጉዝ ሴት ጠቃሚ ነው፡፡ ምርመራው እንዳለቦት የሚያሳይ (ፖዘቲቭ) ከሆነ፣ ከበሽታው ለመፈወስ ነጻ ህክምና ይቀርብሎታል፡፡ እንዳለቦት ማወቁ ሌሎችንም እንዳይበክሉ ያደርጎታል፡፡

## የቂጥኝ ምልክቶቹ ምንድናቸው?

ከብዙ አመታት በፊት በቂጥኝ ተይዘው ከነበር፣ ምልክቱ ሊኖርቦት አይችል ይሆናል፡፡ በቅርቡ የተያዙ ከሆኑ ግን፣ ቂጥኙ የተለያዩ አይነት ምልክቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡ ቂጥኝ ከሌሎች የአባላዘር በሽታዎች በተቃራኒ፣ የሚያቃጥል ስሜት የማይፈጥርና ከመራቢያ አካላት ጋር የተለየ ነው፡፡

የተለመዱት ምልክቶቹ በባክቴሪያ በተጠቃው የሰውነት ክፍል ላይ ህመም አልባ ቁስሎች ይፈጠራሉ፣ ለምሳሌ በመራቢያ አካላት ላይ፣ በጣቶች ወይም አፍ ላይ፡፡ ህክምና በማያደርጉ ግማሽ ያህል ሰዎች ላይ በሽታው በጥቂት ወራት ውስጥ ሌሎች ምልክቶችን ያመጣል፡፡ አብዛኛውም ምልክቶቹ ድካም፣ ሽፍታ፣ መግል የያዘ እብጠትና የጸሁር መሳሳት ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ወደ አንድ ሶስተኛ ገደማ የሚሆኑት በቂጥኝ ከተጠቁ ከብዙ አመታት በኋላ ከባድ ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ ይህም የልብ ህመምና የአእምሮ ህመምን ያስከትላል፡፡

## ከቂጥኝ ህመም እራሴን እንዴት መከላከል እችላለሁ?

እራሴን ቂጥኝ የምከላከልበት መንገድ በሴት ብልት ወይም በፊንጢጣ የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈጸም ኮንዶም በመጠቀም ነው፡
፡

## በቂጥኝ ከተያዝኩ ምን ማድረግ እችላለሁ?

ምርመራው በሽታው እንዳለ የሚያሳይ (ፖዘቲቭ) ከሆነ፣ በአንቲባዮቲክ እንዲታከም ይደረጋል፡፡ ህክምናው ወደ መልካም ጤና እንዲመለሱና ሌሎችን እንዳይበክሉ ያደርጎታል፡፡ ህክምናው መርፌ በመውጋት ይሰጣል፡፡ ብዙ ግዜ ለህክምና ወደ ልዩ ዶክተር መላክ አስፈላጊ ነው፡፡